# የባለ ፊርጁ ብዙ ድሎች መሃንዲስ ሲታወስ!!

/በፀጋይ ሓድሽ welwalo_waw@yahoo.com /

ውድ ባለ ራዕይ መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በድንገተኛ ህመም ከጎናችን ከተለዩ አንድ ዓመት ሞላቸው፡፡ ውድ ባለ ራዕይ መሪያችን ለአገራችን ያበረከቱት አስተዋፅኦ ያለማቋረጥ እየተፃፈና እየተዘከረ ነው፡፡ ለወደፊትም ብዙ ይፃፋል ብዙ ይነገርላቸዋል፡፡ አንደኛ የሙት ዓመታቸው በተለያዩ ዝግጅቶች ለመዘከርና ለማድመቅ የተለያዩ የቅድም ዝግጅት ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ እኛም በዚሁ አጋጣሚ ልናስታውሳቸው ተዝቆ ሰለማያልቀው የልማት አስተዋፅኦአቸው ጥቂት ልንልላቸው ወደደን፡፡




የአረንጋዴው ልማት መሃንዲስ መለስ ዜናዊ ሁሌም ብኩራት እናስታውስዎታለን፣

አንድ በፌደራል ደረጃ የሚታተም ኒውስሌተር ውድ ባለ ራዕይ መሪያችን ከማረፋቸው አንድ ወር አስቀድሞ ታትሞ ነበር፡፡ ኒውስሌተሩ ይዞት የወጣው ቁምነገር በአገራቱዋ የተለያዩ ክልሎች በመከናወን ላይ ያሉት ትላልቅ ፕሮጀክቶች የተመደበላቸው ገንዘብና የአፈፃፀማቸው ሁኔታቸው የሚመለከት ነበር፡፡እነዚህ ትላልቅና የአገራቱዋ እድገት በማፋጠን በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ ያላቸው ፕሮጀክቶች ብውድ ባለ ራዕይ መሪ መለስ ዜናዊ የቅርብ ክትትል ይደረግላቸው እንደነበረ ኒውስሌተሩ በፅሑፉ አስፍረዋል፡፡እኛም እነዚህን ፕሮጀክቶች አጠር ባለ መልኩ በማቅረብ

ለእድገታችን ያላችው ፋይዳና ባለ ራዕዩ መሪያችንና እሳቸው የሚመሩት ድርጅትና መንግስት ምን ያህል ልማታዊ እንደነበሩና እንደሆኑ ለማመልከት እንሞክራለን፡፡

በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የሚገኘው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ መዋጮ የሚካሄድ ሆኖ የፕሮጀክቱ ውል በታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም የተፈረመ ሲሆን የ81 ቢሊዮን ብር በጀት የሚጠይቅ ፕሮጀክት ነው፡፡ ሳሊኒ ኮንትራክተር በተሰኘ ተቋራጭ እየተካሄደ ያለው ይህ ታላቁ ግድብ ስራው የተጀመረው በመጋቢት ወር 2003 ዓ.ም ሲሆን ስራውን ለማጠናቀቅ የተያዘው የጊዜ ሰሌዳ አምስት ዓመት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ህዝብ የተባበረ ክንድ እውን ሆኖ አገራችን ወደ ላቀ የእድገት ጣራ ለመድረስ የጀመረችው በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያግዝ ውድ ባለ ራዕይ መሪያችን "የፕሮጀክቱ የገንዘብ ምንጮች እኛ፣ መሃንዲሶች እኛ፣ሰሪዎቹ እኛ!!" በማለት ካስ ጀመሩት በኋላ ጉልህ ለውጦች ተደርገዉለታል፡፡ ከተደረጉት ጉልህ ለውጦች መካከል የኃይል ማመንጨት አቅም 5,250 ሜጋዋት ወደ 6,000 ሜጋዋት አድገዋል፣የኃይል ማመንጫ ዩኒቶች ብዛት ከ15 ወደ 16 ያደገ እና የፓወር ሃውስ ኤሬክሽን ብዛት ከአንድ ወደ ሁለት እንዲያድግ ተደርገዋል፡፡

ውድ ባለ ራዕይ መሪያችን እንዳሉት የፕሮጀክቱ ግንባታ ለአንድ ቀን እንኳን ሳይቋረጥ በመቀጠል ከጥቂት ግዚያት በፊት የፕሮጀክቱ ትልቅ የስራ ክንውን የሆነው የወንዙ አቅጣጫ የማስቀልበስ ስራ በድል ተጠናቅቆ የግድቡ ዋና ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜም ግንባታው ሃያ ከመቶ በላይ ተጠናቋል፡፡ ለዚሁ ታሪካዊ የልማት ስራ የማይደፈርውን የሚደፍሩና የሚያደፋፍሩ ባለ ራዕዩ መሪና እሳቸው የሚመሩት ድርጅትና መንግስት ትልቅ ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በዚህም ለዘልአለም ይታወሳሉ፡፡

አርጆ ደዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ወጋ፣ ኢሉባቡርና ጅማ ዞኖች የሚገኝ ሲሆን በመንግስት በተመደበ አጠቃላይ ብር 825,141,370 በሚደርስ ወጪ ከየካቲት ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮምያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና በኦሮምያ ውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት የግንባታ ተቆጣጣሪነት ስራው እየተካሄደ ነው፡፡ ስራውን ለማጠናቀቅ የተያዘው የጊዜ ሰሌዳ 540 ቀናት ነው፡፡ ይህም በግንባታ ሂደት ላይ ነው፡፡

የጣናና በለስ የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማት ፕሮጀክት በአማራ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልሎች የሚገኙ ሲሆን፣ከመንግስት በተመደበ እና ከአለም ባንክ በተገኘ ብድርና እርዳታ ብር 1,225,000,000.00 በሚደርስ ወጪ ከግንቦት ወር 2001 ዓ.ም ጀምሮ በህዝብ ተሳትፎ ታጅቦ በመከናወን ላይ ነው፡፡

የርብ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክትና የመገጭ ግድብና መስኖ ፕሮጀክትም በአማራ ብሄራዊ ክልል የሚገኙ ሲሆን፣የርብ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክት በመንግስት በተመደበ ብር 1,336,274,358.08 በመከናወን ላይ ሲሆን፣የመገጭ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ከመንግስት 2,451,953,789.37 ብር በመመደብ እየተካሄደ ነው፡፡

የመቀሌ ከተማ የውሃ መጠጥ ሳኒቴሽን ፕሮጀክትም በብድር፣በእርዳታና በህዝብ መዋጮ በተገኘ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ የሚካሄድ ሲሆን በዚሁ ፕሮጀክት ክንውንም የባለ ራዕዩ መሪ አሻራ አለበት፡፡

በኦሮምያ ክልል የጌዶ-ባኮ መንገድ የ66 ኪ.ሜ መንገድ ስራ በብድር በተገኘ ብር 355,784,706.73 ከጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም ጀምሮ <u>ቻይና ሃይወይ ግሩብ ሊትድ</u> በተባለው የስራ ተቋራጭ ስምምነት ተፈርሞ በመካሄድ ላይ ነው፣በተመሳሳይ መልኩ የኦሮምያው የባኮ-ነቀምት የ65 ኪ.ሜ መንገድ ግንባታ ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር እና ከመንግስት ከተመደበ በጀት ብር 391,167,814.83 በቻይናው የሃይወይ ግሩብ ሊትድ እየተከናወነ ነው፡፡ በትግራይ ክልል የዛሪማ-ማይፀብሪ 70 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው መንገድ ስራ ከብድር በተገኘ ብር 912,631,312.54፣ የማይፀብሪ-ሽረ 68 ኪ.ሜ ርዝመት የመንገድ ስራ መንግስት በመደበው ብር 747,432,284.82 ግንባታ ባለ ራዕዩ መሪያችን ያስጀመሩት ተጠቃሽ የልማት ትሩፋት ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በመደበው ብር 447,279,342.14 በደቡብ ክልል የሚገነባው አላባ-አለም ገበያ-ውልባረግ 58 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው መንገድ፣በኦሮምያ ክልል የሞጆ-አረርቲ 64.5 ኪ.ሜ መንገድ ስራ ከኢትዮጵያ መንግስት በተመደበ ብር 414,485,516.15፣የኢትዮጵያ መንግስት በመደበው ብር 510,670,201.45 የሚገነባው በትግራይ ክልል የሚገኘው የእንዳስላሴ-ደጀና-ዳንሻ 71 ኪ.ሜ መንገድ፣በብር 815,447,361.71 የሚገነባው የእንዳስላሰ-ዓዲረመፅ 77 ኪ.ሜ መንገድ፣ በብር 926,292,277.49 የሚገነባው የዓዲረመፅ-ደጀና-ዳንሻ፣በብር 562,946,553.21 የሚገነባው የ60 ኪ.ሜ ርዝማኔ ያለው የደቡብ ክልሉ የአርባ ምንጭ-ሳውላ(በልታ) መንገድ፣በብር 685,348,315.80 የሚገነባው የ33 ኪ.ሜ ርዝማኔ ያለው የኦሮምያው ጎበንሳ-መተሃራ-ግንደበር መንገድ፣በብር 707,955,759.00 የሚገነባው የ 63 ኪ.ሜ ርዝማኔ ያለው የአፋሩ የአብዓላ-ሻይጉቢ መንገድ ስራ ስናስብ የባለ ራዕዩ መሪያችን ውጤቶች በመሆናቸው ሁሌም ኩራታችን ከፍ ይላል፡፡

አንደ አዲስ አበባ፣ጅማ፣ድሬዳዋ ፣ወሎ/ ደሴ እና ኮምቦልቻ/ ፣ቡሌ ሆራ፣መቱ፣ሆሳዕና፣በመሳሰሉት ትላልቅ የእውቀት ተቋማት የሆኑት ዩኒቨርስቲዎች ብብሊዮን ብሮች በሚገመት ወጪ የሚካሄዱ የማስፋፍያ ስራዎች ስንመለከት “ መተኮስ ካለብን ተኩሰን መግደል ካለብን ድህነትን ነው” የሚለው የባለ ራዕዩ መሪ አስተሳሰብ እውን በመሆን ላይ መሆኑ እያሰብን ኩራታችን እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡

የኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት መንግስት በመደበው ብር 1,278,344,266.44፣የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በብር 11,352,576,940.65 እንዲገነቡ እውን የሆኑት በባለ ራዕዩ መሪ የአመራር ጊዜ መሆናቸው ስናስብ የልሂቃን ልሂቅ የሆኑት ውድ መሪ ምን ያህል የድህነት ጠላት የእድገትና ልማት መሃንዲስ መኖራቸው በጥልቀት እንድንገነዘብ ያስችለናል፡፡

የጅማ እና የኮምቦልቻ አውሮፕላን ማረፍያዎች ግንባታ መንግስት በመደበው በብር 244,137,159.16 እንዲገነባ መታቀዱ ስናስብ፣በተለያዩ ክልሎች የተገነቡ ደረቅ ወደቦች ስናስተውል፣የአገራችን ከተሞች ዋነኛ ችግር የሆነውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለማቃለል ሰፋፊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ግንባቱ መካሄዱንና በመካሄድ ላይ መሆኑ ስንረዳ "አገራችን በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካለቸው አገሮች መካከል ትደርሳለች" ያሉትን እውን የመሆን ጉዞው ፈር እንደያዘ በመገንዘብ ለባለራዕዩ መሪያችን ያለን ክብር ከፍ ከፍ ይላል፡፡ የባለ ራዕዩ መሪ የትግል አጋሮች በሚከተለው መልኩ ያስታዉስዋቸል፡፡

"...መለስ የድህነትን ተራራ ለመናድ የእውቀት ጥይት ያቀበለ መሪ ነው፡፡...መለስ በኢትዮጵያ የአዲሱ የትምህርት ስርዓት ዋነኛ መሃንዲስ ነበር፡፡ የ12ኛ ክፍል መልቀቅያ ፈተናውን በከፍተኛ ማዕረግ ያለፈውና ለዚህም ከአፄ ኋይለስላሴ እጅ ሽልማት እስከመቀበል የደረሰው መለስ በነበረው ብሩህ አእምሮ ጀምሮት በነበረው የህክምና መስክም ይሁን በሌላ በማንኛውም መስክ ትምህርቱ ቢቀጥል ምጡቅ አካዳሚሽያን ሊሆን በቻለ ነበር፡፡እንደማንኛውም በአካዳሚ የመጠቀ ሰው ለግሉና ለራሱ ቢያስብ ኖሮ <u>*በወር ስድስት ሺህ ብር*</u> ደሞዝ እየበላ የሚቀመጥ ሰው ባልሆነ ነበር፡፡የልሂቅም ልሂቅ ሆኖ ሊኖር በቻለ ነበር፡፡ ነገር ግን መለስ ከህዝብ የተነጠለ ልሂቅነትን አጥብቆ የሚጠላ ሰው ነበር ለራሱ በራሱ ጥረት ሁሌም እውቀትን እንደፈለገና እንደሰበሰበ ነገር ግን እርሱ በጥረቱ ያገኘውን እውቀት ህዝቡ በመብትነቱ እንዲያገኘው ያለማሰለስ በትጋት የሰራ ሰው ነው፡፡

በስልጣን ላይ በቆየባቸው በእያንዳንዱ ዓመታት ከድርጅቱ ጋር በመሆን ለአንድ ሚሊዮን ያክል ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ምክንያት ሆኗል፡፡ በየዓመቱ ይህን ያክል ተማሪ ለመቀበል በድምሩ ደግሞ የአገሪቱን አንድ አራተኛ ህዝብ ያክል (20 ሚሊዮን) ለማስተማር የሚያስችል የመምህራን፣የመሰረተ ልማትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት ለማሟላት ያስቻለ እንቅስቃሴ ማካሄዱ በራሱ ትምህርትና እውቀት ለሰው ልጆች እኩል እንዲዳረስ፣ስለዚህም ደግሞ በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ የተሻለ እንዲሆን የነበረውን ሃሳብና ተግባር ያሳያል፡፡ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ብቻ ሳይሆን የሙያና የቴክኒክ ከዚያም አልፎ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በከፍተኛ መጠን የተበራከቱትም በዚሁ በመለስ የአመራር ዘመን ነው፡፡ አገራችን በየመስኩ ተወዳዳሪ ልትሆን የምትችለው ልዩ ልዩ ክህሎቶች ያዳበረ የሰለጠነ የሰው ኋይል ሲኖራት እንደሆነ በማመን የቴክኒክና ቮኬሽናል ስልጠና ማዕከላት በየወረዳው ሳይቀር እነደአሸን

ፈልተዋል፡፡ ከሁለት ዩኒቨርስቲዎች ወደ ሰላሳ ሁለት ዩኒቨርስቲዎች ከመሸጋገራችንም በላይ የአገራችን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት ይቻል ዘንድ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ምሩቃንን ለማበራከት የሚያስችል አቅጣጫ የተቀየሰውም በመለስ አመራር ነው፡፡…"

ባለ ራዕዩ መሪ ልማትና እድገት የሚያስደስታቸው ለዚሁም ወርቃማው እድሜያቸው የሰጡ ሲሁኑ የእድገት ፀር የሆነው መስና በከፍተኛ ሁኔታ አምርረው የሚፀየፉና የሚታገሉ ነበሩ፣የስራ ባልደርቦቻቸው ሰለዚሁ ጉዳይ ይመሰክራሉ፣

"…የፌደራል የስነ-ምግባርን የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደ መሆኑ፣ የሩብ፣የግማሽና ዓመታዊ የስራ አፈፃፀማችን ምን እንደሚመስል በስራ ሂደት ችግሮች ሲያጋጥሙም እነዚያን ችግሮች ለመሻገር ብሎም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ድጋፍ ባሻኝ በማንኛውም ጊዜ አገኛቸው ነበር፡፡ የፀረ-ሙስና ትግሉ በሌሎች ሀገሮች ላይ የሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች እንዳሉ ሁሉ በሀገራችንም ሊያጋጥም እንደሚችል ግንዛቤ በመውሰድ ዕንቅፋቶችን ለማስወገድ ጥረታቸውንና የላቀ ፍላጎታቸውን በማሳየት በርትተው እንድንበረታ የሚያደርጉ መሪ ነበሩ፡፡ከእርሳቸው ጋር የሁለት ጊዜ የስራ ግንኙነት ካደረግን በኋላ ምንግዜም ለውስጤ የምነግረው ትምህርት ቤት እንደምሄድ ነበር፡፡ አሰራር ላይ አመለካከት ላይ ብርሃን የሚፈነጥቁ አዳዲስ ሃሳቦችን እንደማገኝ ግንዛቤ ወስጄ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ሁሉ ግዜ ግንኙነቴን በጉጉት እንድጠብቀው አድርጎኝ ነበር፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጭንቅላት የሚፈልቁ አስተሳሰቦች ጉልበት እንድፈጥር ያደርገኝ ነበር፣ መቼም ቢሆን ከትዝብት ማህደሬ የማይጠፋው ግርምት ሁሉን አወቅ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በሚያፈልቋቸው ችግር ፈቺ አስተማሪና በሚቀይሱት ድንቅ አቅጣጫ ተቋሙን የምመራው እኔ ነኝ ወይስ እርሳቸው?ብዬ መጠየቄን ነው ሲሉ ዛሬም ድረስ ተጣብቷቸው ባለው አድናቆት ተውጠው ይገልፃሉ፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ውይይት ሲደረግ ከአለቃ ጋር የሚደረግ ውይይት አይደለም፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ማንኛቸውንም ጥቃቅን ጉዳዮች አንስቶ ለመወያየት የማይከብዱ ከመሪነት ባህሪ ይልቅ ጓዳዊ ግንኙነታቸው የጠነከረ ከመሆኑም በላይ የሚነሱላቸውን ሃሳቦች አዳብረው አስፍተህ እንድታይ የሚያደርጉ ነበሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተቋሙ ሊያከናውናቸው ከሚገቡ ግዙፍ የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ውስጥ ድርሻው ከተራራው ላይ ቋጥኙን የማስወገድ ያህል ሆኖ ተራራ የሚያክለውን ግዙፍ ችግር ግን ህብረተሰቡና እያንዳንዱ የሴክተር መስሪያ ቤት የሚወጣው እንደሆነ በፅኑ ያምኑ ነበር ይላሉ፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ውይይቶች በምናደርግበት ወቅት ስለ ሙስና ችግሮች በርካታ መፃህፍቶች ያነበቡ ስለመሆናቸው የሚያመላክቱ አስደማሚ ጭብጦችን ያነሱ ነበር፡፡የመንግስት ባለስልጣናት ሐብት ለማስመዝገብ የሚያስችለውን ሰነድ ለማርቀቅ በተዘጋጀን ጊዜ የሳቸው ፍላጎት ከእኛ ዉሱን ፍላጎት እጅግ የራቀ ነበር፡፡የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሐብት እንዲመዘገብና እንዲታይ ከነበራቸው ፅኑ ፍላጎት የተነሳ የሐብት ምዝገባው ሙስናን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን ሐብት ለማወቅም ጭምር እንደሚረዳ በማስረዳት ለስኬታማነቱ ይተጉ እንደነበርም አስረድተዋል፡፡

የሐብት ምዝገባው ሂደት እርሳቸው በፈለጉት መጠን ለማስኬድ አንዳንድ ውስንነቶች (ስጋቶች) እንዳሉ ባስረዳን ጊዜ ባያምኑበትም ሃሳባችንን የተቀበሉት እንዲህ ብለው ነበር ሲሉ የጠቅላይ ሚኒስትር መስስን ንግግር ቃል በቃል ያስቀምጣሉ፣' እኔ የምፈልገው አንድ ቶን ወርቅ ነው ብዬ አንተ ያሰብከውን አላሰናክልም ምክንያቱም አንድ ኪሎ ግራም ወርቅ ያህል ውጤት ሊመዘገብበት ይችላልና ስለዚህ በያዝከው ሀሳብ መሰረት ቀጥል' ይህ ሂደት ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሙሉ ድጋፋቸው እንዳልተለያቸው ይገልፃሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተቋሙን ነፃነት በሚገዳደር መልኩ ' እገሌን ለምን ከሰሳችሁት?እገሌን ለምን አትከሱትም?' እና መሰል ጉዳዮች አንስተው እንደማያውቁና፣ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንኳን ሐብት ቀርቶ የአኗኗራቸውን ሁኔታ እንኳ ምን እንደሚመስል የኢትዮጵያ ህዝብ ተመልክቶታል፡ ፡የመለስ ማንነትና የአኗኗር ሁናቴ ከማንም ያልተለየ ስለመሆኑ ከሞታቸው በስተጀርባ ተመልክተነዋል በማለት ቃለ-ምስክርነታቸው ሰጥተዋል፡ ፡ መለስ ይህ ነው የሚባል በምዝገባ የሚታወቅ ሃብት የላቸውም፡፡ እንግዲህ ወደፊት ታሪክ የሚያወጣቸው እና የሚዘክራቸው በርካታ እውነታዎች ይኖራሉ፡፡ መለስ ምንም አልነበራቸውም፡፡ በሌሎች አገራት ያለውን ተሞኩሮ በምናይበት ጊዜ የፀረ-ሙስና ተቋም የሚያቋቁሙት በሕዝብ ግፊት፣በዕርዳታ ሰጪ አገራት ግፊት እና በዓለምአቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ግፊት ነው፡፡ ታዲያ ሀገራቱ ኮሚሽኑን ሲያቋቁሙም የማስተማርና የመመርመሩን ስልጣን ሰጥተው የመክሰሱን ስልጣን ይነሱታል፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙዎቹ የምርመራ መዝገቦች ሼልፍ ላይ ተቀምጠው እንደሚቀሩ ከአፍሪካ ሀገራት በሚያደርጓቸው የጋራ ምክክሮች መገንዘብ መቻላቸውን ያብራራሉ፡፡

አቶ መለስ ሀገርና ህዝብ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ትልቅ ስራ መስራታቸው፣በተለይ ከህዳሴው በኋላ የማይደፈሩ በርካታ ፕሮጀክቶችን በመድፈር አደፋፍረውናል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጅማሮዎች ግብ ይመቱ ዘንድ ሙሉ አቅማችንን ተጠቅመን ስንረባረብ ራዕያቸውን ስናሳካ ሲታወሱ የሚኖሩበትን እና ወደ ዕድገት የሚያሸጋግረንን ስራ ከወንን ማለት ነው፡፡ የአቶ መለስ ህልም ኢትዮጵያን አልፎላት ማየት ነበር፡፡ ዜጎች ከሚያሸማቅቅ የልመና ተግባር ወጥተን እራሳችንን እንድንችል ነበር፡፡ በሀብታምና በድሃ መካከል ያለው ልዩነት እንዲጠብ የላቀ ፍላጎት ነበራቸው፡፡

መለስ በመሰረታዊነት ሰርቶ፣ለፍቶ፣ደክሞ እንጂ ባለስልጣናትን በሙስና አማልሎ የሚከብር ዜጋ ማየት አይሹም ነበር፡፡ ስለዚህ ይህን ራዕያቸውን ማሳካት ይኖርብናል ለስኬቱ ደግሞ እንደ ዜጋ ልንወጣቸው የሚገቡ በርካታ አደራዎች የተጣሉብን መሆናችን አንዱ ሆኖ እንደ ተቋም የተጣለብንን ኋላፊነት ከሚጠበቅብን በላይ መወጣት እንዳለብን እናምናለን…” ይላሉ ክቡር የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዓሊ ሱሌማን መስከረም 1/2005 ዓ.ም ለታተመው የፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ በሰጡት ቃለ-መጠይቅ፡፡

ባለ ራዕዩ መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአመራር ብቃታቸው ከአገራችን አልፎ አህጉርና ዓለምን የመሰከረለት እንደነበር በቀብር ስነ-ስርዓታቸው ከተነበበው ሰፊ የህወት ታሪካቸው በጥቂቱ አስታውሰን ፅሑፋችን እንቋጫለን፡፡

“…የመለስ የአመራር ሚና እንደ አንድ የድርጅት መሪ እና እንደ አንድ አገር መሪ ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡መለስ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ የመሪነት ሚና መጫወት የጀመረ በአፍሪካ አህጉርም ሆነ በዓለምአቀፍ ደረጃ አክብሮትና አድናቆት የተሰጠው ድንቅ መሪ ነው፡፡ መለስ አጠቃላይ ዓለማቀፍ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን በማጥናትና በመተንተን ብቃት የተካነ መሪ ነው፡፡ በተለያዩ መድረኮች ያሉትን ለውጦች የማጤን፣ ለውጦቹ በትግሉና በአገራችን ላይ የሚኖራቸውን ተፅእኖ የመተንተን፣ በዚያ ላይ ተመስርቶም ለትግሉና ለአገራችን የሚበጁ አቅጣጫዎችን የመቀየስ አቅም አለው፡፡ በትምህርትና ምርምር ባካተው እውቀት የአለምን የሃይል ሚዛንና አሰላለፍ፣ የአፍሪካን ጂኦ ፖለቲካዊ ክብደት፣የአለምን ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር፣የዓለምአቀፍ ተግዳሮቶችን ባሕርይና እነዚህ ሁሉ በአፍሪካም ሆነ በአገራችን ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ ይመረምራል፡፡ ከዚህ የሚገኙ ውጤቶችም መሰረት በማድረግም አዎንታዎ አዝማሚያዎችን ይመረምራል፡፡ ከዚህ የሚገኙ ውጤቶችም መሰረት በማድረግም አዎንታዎ አዝማሚያዎችን ለማጠናከርና ለመጠቀም አሉታዊ አዝማሚያዎችን ደግሞ ተፅእኗቸውን ለመቀነስና ለመመከት የሚያስችሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያመነጫል፡፡

መለስ ከቅርብ አመታት ወዲህ የአፍሪካ ድንቅ ልጅ የሚል ስያሜ ያተረፉለትን የተለያዩ ተግባራት አከናውኗል፡፡ የአፍሪካ ምርቶች ዋጋ እንዲሻሻል፤ ወደ አፍሪካ የሚፈሰው ኢንቨስትመንት፣ ብድርና እርዳታ እንዲጨምር፤ አፍሪካውያን በአየር ንብረት መዛባት ለሚደርስባቸው ጉዳት ማካካሻ እንዲያገኙ እንዲሁም የአለም የንግድ ስርአት ለአፍሪካ ዕድገት የሚያመች እንዲሆን ለማድረግ በተገኙት መድረኮች ሁሉ ታግሏል፡፡

የአፍሪካውያን ጥቅም የሚረጋገጠው በተናጠል በሚደረግ መፍጨርጨር ሳይሆን በመሰረታዊ የጋራ ጥቅም ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም በመያዝ፣ በዓለምአቀፍ መድረኮች በአንድ ድምፅ በመሰለፍ

መሆኑን መለስ ከልቡ ያምናል፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት ከአፍሪካውያን መሪዎች ጋር በመመካከርና ጠቃሚ ሃሣቦችን በማቅረብ ተቀባይነትንና አክብሮትን አትርፏል፡፡

መለስ የአካባቢው ሀገሮች ያለን እድል ተሳስረንና ተባብረን መልማትና ማደግ ነው የሚል ጽኑ እምነት አለው፡፡ አገራችንንና የአካባቢውን አገሮች በመሰረተ ልማት ለማስተሳሰር ቆራጥ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በአባይ ወንዝ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ላይ ያራመደው አቋም ለዘመናት በአካባቢው ሰፍኖ የቆየውን ኢ-ፍትሃዊ አስተሳሰብ የሸረሸረና የጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ በተፋሰሱ አገሮች ዙሪያ ተቀባይነት እንዲያገኝ ውጤታማ ስራ የሰራ ጠንካራ መሪ ነው፡፡ መለስ ከሁሉም ጐረቤቶቻችን ጋር በሰላም፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ማድረግ ዞሮ ዞሮ ጠቀሜታው ለኛ ነው የሚል የፀና አቋም አለው፡፡

በድርድርና በውይይት ሊፈታ ያልቻለ እንዲሁም በህዳሴ ጉዟችን ላይ የተጋረጠ እንቅፋት ካልሆነ በቀር በምንም አይነት መልኩ ከጐረቤቶቻችን ጋር ወደ ግጭት መግባት የለብንም፤ ሲሆን ሲሆን ‘ከመንገዳችን ወጥተንም’ ቢሆን ለጐረቤቶቻችን ሉዓላዊነትና ብሄራዊ ጥቅም መስራት አለብን የሚል ቁርጠኛ አቋም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አራምዷል፡፡

እነዚህ የመለስ አፍሪካዊ አቋሞች በተቋም ደረጃ እንዲፈፀሙ በራሱ ሃሣብ አመንጪነትና ግንባር ቀደም ተሳትፎ ተመስርቶ ውጤታማ ተግባር ያከናወነው የኔፓድና የኢጋድ ተቋማት ለዚህ ምስክር ናቸው፡፡ መለስ በአፍሪካ ህብረት ደረጃም አገራችን የፅ/ቤቱ መቀመጫ እንድትሆን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ጥቅም ለማራመድ የሚያስችሉ አቋሞችን የሚወስድ ተቋም እንዲሆን ያለ መታከት ሰርቷል፡፡ በተለይም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የአፍሪካን ድምፅ በማስተጋባት የአፍሪካ ቃል አቀባይ (Spokesman of Africa) የሚል ስያሜ ያገኘ ድንቅ የአፍሪካ ልጅ ነው፡፡

በተደጋጋሚ በG-8 እና በG-20 ስብሰባ ላይ አፍሪካን ወክሎ እንዲገኝ የሚጋበዘው መለስ በኮፐንሃገን፣ ደርባንና ዳቮስ ላይ በተካሄዱት የመሪዎች ስብሰባ ላይ የአፍሪካን ጥቅሞች በመወከል ያደረገው ክርክር አንቱታን አትርፎለታል፡፡

ይህ አካሄድ ለዘመናት አፍሪካ በእንደዚህ አይነት መድረኮች የነበራትን የተሰፈኝነት ሚና የቀየረና አፍሪካን ወደ ተደራዳሪነት ያሸጋገረ በመሆኑ ለአፍሪካ አዲስ ምዕራፍን የከፈተ ነበር፡፡

መለስ በአፍሪካውያን ዘንድ በአድናቆት ከሚነሳባቸው ጉዳዮች አንዱ ለአፍሪካ ሰላም ያደረገው አስተዋፅኦ ነው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታትና መግባባትን ለመፍጠር የተጫወተው የአደራዳሪነትና የግጭት አፈታት የመሪነት ሚና በእጅጉ የሚደነቅ ነው፡፡ መለስ በአፍሪካ ደረጃ በሶማሊያ፣ በሱዳን፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲና በላይቤሪያ ሰላም እንዲሰፍን አገራችን የድርሻዋን እንድትወጣ በአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ዘንድ የሚወደስ ሰላም የመፍጠርና የሰላም ማስከበር ተልእኮዎችን በፍፁም አፍሪካዊ መንፈስ ሲመራ የኖረ ታላቅ አፍሪካዊ መሪ ነው፡፡

መለስ በዓለምአቀፍ መድረኮች ከሌሎች የአለም መሪዎች ጋር የሚያደርጋቸው ውይይቶች ከፍተኛ አክብሮትን አትርፈውለታል፡፡ እጅግ በሳልና አንደበተ ርቱዕ ነው በማለት የሚገልፁት ታላላቅ የአለም መሪዎች መለስ የአገራችንን ልማት ለማፋጠን፣ ለአካባቢያችን ሰላምና መረጋጋት፣ ለሚያደርገውን እንቅስቃሴና ለፀረ-ሽብርተኝነት አቋሙ አድናቆታቸውን ይገልፃሉ፡፡ በግል ባህሪው፣ በታታሪነቱና በአቋም ፅናቱም ያወድሱታል፡፡ በአመራር ብቃቱ የአገራችንን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ህዳሴ እውን ለማድረግ የሚታገል የአፍሪካ ታላቅ መሪ መሆኑንም አበክረው ይገልፃሉ፡፡

መለስ ለብዙዎች በእጅጉ የሚያስደንቅ ጠንካራ ሰብእና እንዲኖረው፣በወጣትነቱ የመሪነት ክህሎት እንዲላበስ እና ዘርፈ ብዙ ጥንካሬዎችን እንዲያካብት ያደረገው ምንድ ነው ብለው የሚጠይቁ በርካቶች ይኖራሉ፡፡መለስን መለስ ያደረጉ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ማንነቱን ሲቀርፁ የኖሩ በርካታ ከባቢያዊ ምክንያቶች የመኖራቸውን ያህል የተለዩ የግል ባህሪያትም አሉት፡፡ ሁሉንም ምክንያቶች መዘርዘር ቢያዳግትም ጉላ ያሉትን መጥቀስ ግን ይቻላል፡፡

እንደማንኛውም ታጋይ ሁሉ መለስ የድርጅቱ የህወሓት/ኢህአዴግ ውልድ ነው፡፡ መለስ መለስ ሊሆን የቻለው በውይይት በሚያምን፣ በተመሳሳይ አቋም የተሰለፉ አባላትን ባቀፈ፣ ህዝቡንም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ባሰለፈ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በመታቀፉ ነው፡፡ መለስም በተደጋጋሚ እኔን የፈጠረኝ ኢህአዴግ ነው በማለት የርሱ መሰረታዊ እሴቶች ከኢህአዴግ መሰረታዊ እሴቶች የተቀዱ መሆናቸውን ይገልፅ ነበር፡፡ መለስ የድርጅቱን ዓላማዎች የህይወቱ መመሪያ አደረጋቸው፡፡ ኢህአዴግን ከመሰለ ድርጅት ውጪ መለስን የመሰለ ሰው ይፈጠራል ብሎ ማሰብ የሚቻል አይሆንም፡፡ ይህን ከድርጅቱ የወረሰውን ስብእና አጐልብቶና አጠናክሮ በመግለፅ እንዲሁም የራሱን የግል ስብዕና ለድርጅታዊ ተልእኮው በማስገዛት መለስን መለስ ሊያደርገው የቻለው ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

መለስ የላቀ ህዝባዊ ፍቅር ያለው መሪ ነው፡፡ ይህ ጥልቅ ህዝባዊ ፍቅር መለስ እያንዳንዱን ጉዳይ ከህዝቦች ጥቅም አኳያ እንዲመዝን አድርጐታል፡፡ የህዝቦች ሰቆቃ የሚያንገፈግፈው፣ ለህዝቦች ጥቅምና ደህንነት ቀን ከሌት የሚጨነቅ ይህንን ፍቅሩን የሁሉም ተግባራቱ አንቀሳቃሽ ሞተር

አድርጐ የሚጠቀም መሆኑ መለስን መለስ አድርጐታል፡፡የህዝቦችን ፍላጐት የሚያነፈንፍ ለህዝብ የቀረበ ልብ አለው፡ለኔ አገር ማለት ህዝብ ማለት ነው፡፡የአገር ፍቅርም ማለት ከህዝብ ፍቅር ውጪ ትርጉም የለውም ይላል መለስ፡፡ህዝብ በትክክለኛ ድርጅት ከተመራ ታሪክ ሊሰራ የሚችል መሆኑን አምኖ ወደ ጥቅሙ የሚያመራውን አቅጣጫ ለማስያዝ መለስ ሁልጊዜ ይጥራል፡፡

መለስ ለብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች-ለአገራችን አርሶአደሮች እና አርብቶ-አደሮች -ወገንተኝነቱ የጐላ ነው፡፡ የአገራችንን መፃኢ ዕድል የሚወስነው በአርሶ አደሩ ህይወት ላይ የምናመጣው ለውጥ ነው ብሎ ያምናል፤ አጠንክሮም ይሰራል፡፡

መለስ ለሴቶችና ለወጣቶች ያለው ወገንተኝነትም ከፍተኛ ነው፡፡ ወጣቱን እውቀት እናልብሰው፣ ድህነትን የማጥፊያ አቅጣጫ እንጠቁመው፣ መጪዋን ኢትዮጵያ የሚረከብበት ጉልበት እንዲያገኝ እንገንባው ይላል፡፡ የህዝቦች የነፃነት ደረጃና የሃገራትም የዕድገት ልክ የሚመዘነው በሴቶች የነፃነትና የተጠቃሚነት መጠን ነው የሚል ዕምነት አለው፡፡ ሁልጊዜ ሴቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አቅጣጫ ይማትራል፡፡ በአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅና ድንበር፣ ዘር፣ ፆታ፣ እምነት ባልገደበው ሁኔታ የመላ አገሪቱን ህዝቦች ፍቅር የተጐናፀፈው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

መለስ የማይናወጥ የዓላማ ፅናት ያለው መሪ ነው፡፡ መለስ ላመነበት ዓላማ በቁርጠኝነት እስከመጨረሻው የሚታገል መሪ ነው፡፡ ያሰበውንና ያለመውን ጉዳይ ለማሳካት የሚያስችል የታመቀ ውስጣዊ ሃይል አለው፡፡ እያንዳንዱን ጉዳይ ከተነሳበት ዓላማና ከጨበጣቸው መርሆዎች አኳያ ይመዝናል፡፡ ከሰዎች ባህሪ አምርሮ የሚጠላው መርህ አልባነትን ነው፡፡ መለስ በቀጣይነት የሚማር የተማረውንም ለተነሳበት ዓላማ የሚያውል መሆኑ ሌላው የርሱ መገለጫ ነው፡፡ መለስ ያነባል፣ ይጠይቃል፣ ያዳምጣል፣ ያጠናል፣ ያወቀውን ያሳውቃል፣ ዕውቀቱን ተግባር ላይ ያውላል፤ ከተግባሩም ይማራል፡፡ ይህ የማያቋርጥ የመለስ የእንቅስቃሴ ምህዋር ነው፡፡

መለስ በእንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖር ነው፡፡ ሁልጊዜም በተግባራዊ እንቅስቃሴ ወስጥ ተጠምዶ ይኖራል፡፡ ከተግባራት ውስጥ ቁልፉን ጉዳይ ለይቶ እዚያ ላይ ይረባረባል፡፡ ከማነቆዎችም ዋነኞቹን ለይቶ እነርሱን ለመፍታት ሙሉ አቅሙን ይጠቀማል፡፡ መለስ ማንም ከሚገምተው በላይ በሁሉም ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃ አለው፡፡ እንዳንዴም መረጃው ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ከሚገመቱት ሰዎች በላይ መረጃ ኖሮት ይገኛል፡፡ በእንቅስቃሴ ውስጥ ሁሉም ነገር መፍትሄ ይኖረዋል ብሎ ያምናል፡፡

ዋነኛውና ትልቁ የመለስን ባህሪ የቀረፀው በድህነት ላይ ያለው የመረረ ጥላቻ ነው፡፡ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛው ፀረ ድህነት ትግሉ ነው፡፡ የአገራችን ህዝቦችም ሆኑ መላው የአፍሪካ ህዝቦች ድህነት አይገባቸውም በማለት ከድህነት መውጫ ቀዳዳ ሲያማትር ዕድሜውን ሙሉ አሳልፏል፡፡ መለስ ድህነት ባለበት ሁኔታ የአገር ሰላም ሊረጋገጥ አይቻልም፣ ዴሞክራሲም ሊሰፍን አይችልም፣

እንዲያውም ድህነት የዜጎችን ሰብአዊነት እና ክብር የሚደፍቅ ነቀርሳ ነው የሚል የፀና እምነት ነበረው፡፡ መላ ህይወቱን በትግል ሲንጠው የነበረው ይኸው ፀረ-ድህነት ጠንካራ አቋሙ ነው፡፡…”

በባለ ራዕዩ መሪ ብልህ አመራር በጤና፣በትምህርት፣በመንገድ እንዲሁም በዴሞክራሲና ሰላም የተመዘገበው ውጤት የንግድና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው ውጤታማ እንዲሆን ታላቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ በባለ ራዕዩ መሪ የአመራር ብልህነት በመገናኛ ኢንዱስትሪው የተመዘገበው አመርቂ ውጤት የንግድና የኢንሰትመንት ስራው በማቀላጠፉ በኩል ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአረንጋዴው ልማት መሃንዲስ መለስ ዜናዊ ድሎች በርካታ ናቸው፣ ስለዚህም “ የአረንጋዴው ልማት መሃንዲስ ቃልህ ይጠበቃል” ብለን ስንዘክራቸው ያስጀመሩዋቸውን ድሎች እንደምናስቀጥል እርግጠኞች በመሆን ነው፡፡